# ሰንደቅ፡ዓላማችን፡የመታዎቂያችን፡መሠረተ፡ምልክት፡ናት።

ማክሰኞ፣ጳጉሜ፡፩፡ቀን፡፪ሺ፫፡ዓመተ፡ምሕረት።

ክፍል፡፪፤



“ዝምም፡ባለ፡አፍ፡ዝምብ፡አይገባበትም”

“ወይ፡ሀገሬ!”፡ብለህ፡እንዳልዘፈንህ፤
ዛሬ፡የወያኔ፡ጎረደማን፡ሆንህ።

## በል፡እንካ!፤

ሀገርክን፡በመክዳት፡ሆድህን፡የወደድህ፣
ከዕውነት፡የሸሸህ፡፣ለጥቅም፡የሰገድህ፤
ወገን፡ረሃብተኛ፡መሆኑን፡የማታይ፣
በጉራ፡በማበድ፡በውሸት፡ሰው፡ደላይ፣
የተናገርከውን፡ያውም፡ባደባባይ፣
ለዋዋጭ፡እንደስስት፡ቀፈታሙ፡አባይ፣
ሰሎሞን፡ተካልኝ፡ቂሎ፡አይደለህም፡ወይ!።
ትርጉሙ፡ሳይገባህ፡የዘፈንከውን፣
እስቲ፡አስነብብና፡ይታዘቡን፡እኛን፣
ያለ፡አግባብ፡ሲትዘልፈው፡አማሪ፡ታማኝን፣
ስሕተት፡በመሆኑ፡የተቸንበትን፣
በቧልታ፡በዋልታ፡የተናገርከውን።

## “ወይ፡ሀገሬ!”፣..................

“ምን፡ነካሽ፡ሀገሬ፣ወገኔን፡ምን፡ነካው፣
አባት፡የሰጠውን፡መሬቱን፡ያስነካው፤
ደሙን፡ለነፃነት፡አፍስሶ፡ለምድርሽ፣
ምን፡ይላል፡ያ.....ልጅሽ፡ቀና፡ብሎ፡ቢያይሽ፣
ተቆርሰሽ፣ተቆርሰሽ፡እያነሰ፡አካልሽ፣
ያ.....ጀግና፡ቢሰማ፡ሀገሬ፡ምን፡ይልሽ።
ዛሬ፡ባድሜን፡ነው፡ይቀጥላል፡ገና፣
አንጠራጠርም፡ትናንት፡ታይቷልና።
ባድሜን፡ለመስጠት፡መሞት፡ለምን፡አሻን፣
የመጣን፡ካልሆነ፡ለማጥፋት፡ሀበሻን።

“ወይ፡ሀገሬ!”............................፤

መሬት፡እንደ፡ዳቦ፡ሸንሽኖ፡እያደለ፣
ውዱን፡ያገሬን፡ልጅ፡ስንቱን፡አስገደለ።
ቃል፡ኪዳንን፡ላይተው፡የመገንጠል፡ሱሱን፣
ትንሽ፡አዘናግቶን፡ቀጠለው፡ማፍረሱን።
ወጣት፡እንደ፡ቅጠል፡ሲረግፍ፡ለሀገሩ፣
እኛን፡መቀነስ፡ነው፡ለሱ፡ቁም፡ነገሩ።
ምን፡ነካሽ፡አገሬ፡ምን፡ነካው፡ጀግናው፡ሰው፣
ታንክና፡አውሮፕላን፡ጣሊያን፡ያልመለሰው፣
ለመንጠቅ፡ለመግዛት፡የመጣ፡ባዳ፡ነው፣
ጣሊያንም፡ላፈርሽ፡ይኸም፡ለምድርሽ፡ነው።
እንዋጋ፡እያለ፡ሲኖር፡ተመሳስሎ፣
ልቡ፡ከወዲያ፡ነው፡እኛን፡አስገድሎ።
“ወይ፡ሀገሬ!”.......................፤
“ምን፡ነካሽ፡ሀገሬ፣ወገኔን፡ምን፡ነካው፣
አባት፡የሰጠውን፡መሬቱን፡ያስነካው፤
ደሙን፡ለነፃነት፡አፍስሶ፡ለምድርሽ፣
ምን፡ይላል፡ያ......ልጅሽ፡ቀና፡ብሎ፡ቢያይሽ፣
ተቆርሰሽ፣ተቆርሰሽ፡እያነሰ፡አካልሽ፣
ያ.......ጀግና፡ቢሰማ፡ሀገሬ፡ምን፡ይልሽ።
ዛሬ፡ባድሜን፡ነው፡ይቀጥላል፡ገና፣
አንጠራጠርም፡ትናንት፡ታይቷልና።
ባድሜን፡ለመስጠት፡መሞት፡ለምን፡አሻን፣
የመጣን፡ካልሆነ፡ለማጥፋት፡ሀበሻን።
“ወይ፡ሀገሬ!”፤“ወይ፡ሀገሬ!”፤“ወይ፡ሀገሬ!”፤“ወይ፡ሀገሬ!”፤“ወይ፡ሀገሬ!”፤.............
እንደ፡ልጅ፡ጨዋታ፡ሰኞና፡ማክሰኞ፣
ሀገር፡ገዛሁ፡ይላል፡ወይ፡ሞኞ!፣ወይ፡ሞኞ!።
ዝምታው፡ፍርሃት፡ከመሰለህ፡ጀግና፣
ተመከር፡እባክህ፡ታሪክ፡ጠይቅና።
የተኛው፡አንበሣ፡ከንቅልፉ፡ሲነቃ፣
መሸሸጊያም፡የለ፡ምድርም፡አትበቃ።
ታጋሽና፡አስተቃይ፡ቢሆንም፡ሐበሻ፣
ሲበቃው፡ወዮልህ፡ያሳጣል፡መድረሻ።
ያ.................................ሳጣል፡መድረሻ።

“ወይ፡ሀገሬ!”.........................፤

“ምን፡ነካሽ፡ሀገሬ፣ወገኔን፡ምን፡ነካው፣
አባት፡የሰጠውን፡መሬቱን፡ያስነካው፤
ደሙን፡ለነፃነት፡አፍስሶ፡ለምድርሽ፣
ምን፡ይላል፡ያ.....ልጅሽ፡ቀና፡ብሎ፡ቢያይሽ፣
ተቆርሰሽ፣ተቆርሰሽ፡እያነሰ፡አካልሽ፣
ያ......ጀግና፡ቢሰማ፡ሀገሬ፡ምን፡ይልሽ።
..........................“ወይ፡ሀገሬ!”፤“ወይ፡ሀገሬ!”፤
“ወይ፡ሀገሬ!”፤“ወይ፡ሀገሬ!”፤“ወይ፡ሀገሬ!”፤...
እያልህ፡እንዳልዘፈንህ፡ሁላ!!!!።

ከዜናማርቆስ፡መርሐ፣ካናዳ፤
እ፡ጦማር፡- zienamarqos@yahoo.com

EthioLion.Com

Ethiopia Will Prevail!